# “የሚፈርስ ከተማ ፤ ነጋሪት ቢጎሰም አይሰማ”

ከአይምሮ ዳኛቸው

የህዝብ አመጽና አልገዛም ባይነት መቼና እንዴት ሊነሳ እንደሚችል ለመተንበይ ያዳግታል ። ሆኖም ግን ጭቆናና አፈና በተንሰራፋበት አገር ሕዝባዊ አመጽ በማናቸውም ጊዜ ሊገነፍል እንደሚችል የሚጠቁሙ በርካታ አመላካች ሁኔታዎች ይኖራሉ ። እነዚህ አመላካች ሁኔታዎች በሚታዩበት ስፍራ ሁሉ ሕዝብ አሻፈረኝ ፤ አልገዛም ፤ በማለት አምርሮና ተቆጥቶ ሊወጣ የሚችልበት ወቅት እሩቅ እንደማይሆን ግን መናገር ይቻላል ።

አምባገነኖች በተፈጥሯቸው ሊማሩ የሚችሉ ባለመሆናቸው አንደኛው አምባገነን ካንደኛው አወዳደቅ ምንም አይማርም ። በመሆኑም ለዘመናት ሲረግጡት የቆዩት ሕዝብ ፣ ስብዕና የሌለው ግዑዝ ፍጥረት ፣ ለአመፅ የማይነሳ ፤ ለለነሱ መኖርና ለለነሱ እራሱን ማስተዳደርም ሆነ መምራት የማይችል አድርገው ያዩታል ። ይህን የተሳሳተ ግምት እራሳቸውን በራሳቸው አሳምነው በቅዠት ዓለም ስለሚዳክሩ ፣ እነሱ ቢያልፉም እንኳን በአጽማቸውም ሊገዙት የሚችሉ እስከሚመስላቸው ድረስ ልባቸው በትዕቢት ይደፈናል ፣ ይደነቁራል ። ከዚህ ከጨለምተኛ አስተሳሰባቸው የተነሳ ዘወትር አወዳደቃቸው ውርደትን ያካተተ እንደሆነ ታሪክ በተደጋጋሚ አስተምሮናል ። ዛሬም በሰሜን አፍሪካ እየተንኮታኮተ ያለው የአምባገነኖች ውድቀት የሚያስተምረን ይሄንኑ የተደጋገመ ታሪካዊ ሃቅ ይሆናል ።

በቱኒዝያ የቤን አሊ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለ23 ዓመት ህዝብን ሲጨቁንና ሲመዘብር ፣ በማን አለብኝነትና በትዕቢት ተወጥሮ ለዘመናት ህዝብን እንዳልበደለና እንዳላሰቃየ ሁሉ “ታሪክ እራሱን ይደግማል” እንዲሉ የሱም ዕጣ ፈንታ ደርሶ እንደ አንበሳ ይንጎማለል የነበረው ቤን አሊ ዛሬ ዝናብ እንዳበሰበሳት ውሻ ጭራውን ከኋላው ወሽቆ የሀፍረት ማቁን ተከናንቦ በማይገታው ሕዝባዊ አመጽ ተሸቀንጥሮ ከሕዝብ ጫንቃ ላይ ላንዴም ለሁሌም ተወግዷል ።

የቱኒዝያ ሕዝብ ለዘመናት በጫንቃው ላይ ተሸክሞት የኖረው የቤን አሊ አገዛዝ በሕዝብ ላይ ያደርስ በነበረው አፈናና ጭቆና ፣ ሕዝብ በነፃነት መደራጀት አለመቻል ፣ የሰባዊ መብት መረገጥ ፣ የሥራ አጥነት ፣ የኑሮ ውድነትና የመሳሰሉት ለዚህ አምባገነን አይነተኛ መገለጫ ባህሪዎቹ ነበሩ ። ይህንንም ሕዝባዊውን አመጽም ያነሳሳው የአንድ ጀንበር ክስተት ሳይሆን የጭቆናው አስከፊ ገጽታ ለ23 ዓመታት ስር ሰዶ የነቀዘና የበሰበሰ በመሆኑ ነው ።

“ለሁሉም ጊዜውን ይጠብቅለታል” እንደሚባለው ለዚህ የቱኒዝያ ሕዝባዊ አመጽ አነሳሽ በመሆን የሚጠቀሰው አንድ የኮሌጅ ምሩቅ የሆነ ወጣት ስርአቱ በፈጠረው የገለማ አስተዳደር የተነሳ ሥራ ማግኘት ባለመቻሉ እራሱንና ቤተሰቡን አሸንፎ ለማደር በመንገድ ላይ የአትክልት ንግድ ተሰማርቶ እየሰራ ሳለ የስርአቱ አገልጋይ በሆኑ የፖሊስ ሰራዊት አባላት የንግድ ፈቃድ የለህም በማለት እንዳይነግድ ከማድረጋቸው ባሻገር ድብደባም በመፈጸማቸው ወጣቱ በፖሊሶቹ አድራጎትና በስርአቱ እጅግ በመማረሩ እራሱን በእሳት አቀጣጥሎ ህይወቱን ያሳልፋል ። ይህ ጭካኔ የተሞላ ድርጊት የቱኒዝያን ሕዝብ እጅግ ስላስቆጣው በሕዝብ ውስጥ ታምቆ ለዘመናት የቆየው አልገዛም ባይነት ሳይታሰብ በድንገት ከዳር እስከዳር ተቀጣጥሎና ተንቦግቡጎ በመነሳቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ የቤን አሊን አምባገነን መንግሥት ከስሩ ነቅሎ ለመጣል አስችሎታል ።

የግብፅን ሁኔታንም ስንመለከት ለ30 ዓመት ሕዝብን አፍኖ ይዞ የነበረው የሙባረክ አምባገነናዊ አገዛዝም ዛሬ አንድ እግሩን መቃብር አስገብቶ ግብአተ መሬቱን እየጠበቀ እንደሆነ ሁላችንም የዓይን ምስክሮች እንድንሆን አብቅቶናል ።

በነዚህ ሁለት የሰሜን አፍሪካ አገሮች የተካሄደው ሕዝባዊ አመጽ እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጥሎ ወደ አጎራባች አገሮችም በመዛመቱ የተነሳ በቅርቡም በጆርዳን ፤ በየመን ፣ በሱዳንና በመሳሰሉት አገሮችም ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች የታዩ መሆናቸው ተዘግቧል ፤ ለሚያደርጉትም ህዝባዊ ትግል የተሳካ ይሆንላቸው ዘንድ “የነፃነትን ናፋቂ” ዜጎች ሁሉ ጽኑ ምኞት ነው ።

ወደሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ ፣ ዛሬ አመጽ እያካሄዱ ባሉት አገሮችና ባገራችን መካከል ያለው የጭቆና አገዛዝ በብዙ መልኩ ተመሳሳይ ቢሆንም የአገራችን ሁኔታ ግን ከነዚህ አገሮች ሁኔታ እጅግ የከፋ ነው ። ይህን መሰል ሕዝባዊ አመጽም በኢትዮጵያ ውስጥ መካሄድ የነበረበት በነዚህ አገሮች አመጽ ከመካሄዱ አመታት ቀደም ብሎ እንደነበር አይካድም ። ነገር ግን በቱኒዝያና በግብጽ የተነሳውና አምባገነኖችን ያንበረከከው ሕዝባዊ አመጽ በአገራችንም ቢደረግ ተመሳሳይ ውጤት ያስገኛል ወይንም ይሰራል ማለት አይደለም ።

በአገራችን ያለው አምባገነናዊ አገዛዝ ከነዚህ ሁለት አገሮች አምባገነኖች ጋር ሲነፃፀር በአይነቱ እጅግ የከፋ ብቻ ሳይሆን አገዛዙ በዘር የተደራጀና የአንድ አናሳ ብሄር ተቋምም ጭምር ነው ። በመሆኑም ዜጎች በአገራቸው እንደ አንድ አገር እንዲደራጁ የማይፈቅድ ፣ ህዝብ በሀገር ደረጃ ሳይሆን በዘር እንዲደራጅ የሚገፉና የሚያበረታታ ፣ መገንጥልና መበታተንን አላማው አድርጎ ክልልን የፈጠረ ፣ ህዝብ እንደ አንድ አገር በአንድ በሰንደቅ አላማ እንዳያምን የሚሰብክ ፣ የአገርና የአንድነት መለያው የሆነውን ሰንደቅ አላማውን የሚያናንቅ ፣ በሌላ መልኩ ደግሞ ክልል ብሎ ለፈጠራቸው የጎሳ አጥሮች የየራሳቸው መለያ የሆነ የቃሊቻ ሸርጥ የመሰለ ሰንደቅ አላማ በማደል መለያቸው እሱና እሱ ብቻ እንደሆነ ለዓመታት የሰበከ ፣ መርዘኛ የሃይማኖት ልዩነቶችን በማራገብና በመቆስቆስ ለዘመናት ተከባብሮና ተፋቅሮ በሚኖር ህዝብ መሃከል መጠራጠር ፣ መሻከር እንዲኖር ያደረገ በመሆኑ ከነዚህ ሁለት አገሮች ከነበሩት አምባገነን አገዛዞች ባያሌው የተለየ የሚያደርጉት መለያ ባህሪያቶቹ ናቸው ።

በመሆኑም በቱኒዝያና በግብጽ የተደረገው አመጽ በአንድ አገር ፣ በአንድ ህዝብ ፣ በአንድ ሰንደቅ አላማ የታጀበ ፣ በሰንደቁና በአንድነቱና በሚኮራ ህዝብ የተቀነቀነና የተሰባሰበ በመሆኑ የማይቀረውን ህዝባዊ ድል በአጭር ጊዜ እንዲቀዳጅ አስችሎታል ።

ያም ማለት ኢትዮጵያዊው በአንድ አገርና በአንድ ሰንደቅ አላማ አያምንም ማለት ሳይሆን ፣ ይህ የጎጠኞች አገዛዝ ለሃያ አመት የለፋበት ኢትዮጵያን የማፈራረስና የመበታተን አላማው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በአንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደማጭነትን ያገኘና የጠለፋው ሰለባ ስለሆነ ባገራችን ውስጥ በአሁኑ ወቅት በቱኒዚያና በግብጽ የተደረገው አይነት ህዝባዊ አመጽ ቢነሳ ተጠቃሚው በኢትዮጵያ አንድነትና በአንድ ሰንደቅ አላማ የሚያምነው ህዝብ ሳይሆን የሚጠቀመው በግንጠላ መርሆ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው እንደ ኦብነግና (ONLF) ኦነግ (OLF) የመሳሰሉት ጸረ ህዝብ ፣ ጠባብ ብሄርተኞች እንደሚሆኑ ከማንም የተሰወረ አይሆንም ።

የዛሬ ዓመት ገደማ የወያኔ ቁንጮ መለሰ ዜናዊ ሎንዶን ከተማ በመጣበት ወቅት እሱን ለመቃወም የተደረገውን ህዝባዊ ሰልፍ በመመልከት ብዙ ማለት ይቻላል ። ሰልፉ የተዋጣለትና የተሳካ ነበር ቢባልም በአንፃሩ ግን በአንድ ኢትዮጵያ ፣ በአንድ ህዝብ ፣ በአንድ ሰንደቅ አላማ የሚያምነውን አገር ወዳድ ግን እጅግ ያሳዘነ እንደነበር ከማንም የተሰወረ አልነበረም ። ሰልፉን ከተካፈሉት መሃል በአንድ ኢትዮጵያ የሚያምኑት የኢትዮጵያ መለያ የሆነውን አረንጓዴ ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት ያለውን ሰንደቅ ይዘው ሲወጡ ፤ ኢትዮጵያዊነታቸውን የካዱና ፣ ኢትዮጵያ በቅኝ ገዢነት ይዛናለች የሚሉ የተገንጣይ አቀንቃኞች በፊናቸው ከቀረው ኢትዮጵያዊ እራሳቸውን ገንጥለው ወያኔ የወረወረላቸውን እራፊ በማንገብ ኦነጉ የኦነግ መለያ የሆነውን ኦጋዴኑ የኦጋዴን መለያ የሆነውን ቡቱቶ ይዞ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ተስፈንጥሮ መሰሎቹን አሰባስቦ አሳዛኝ ትዕይንቱን ያሳየበት ወቅት ነበር ።

ታዲያ ይህንን አፍራሽ አላማ ያነገቡና የገዛ አገራቸውን እንደ ባዕድ አድርገው የሚመለከቱ የምዕራቡና የአረብ ፍልፈሎች በአንድነታችን ላይ ጥላ አጥልተው አገራችንን ለማፈራረስና ለመበታተን ምለው ተገዝተው ፣ መሳሪያ አንስተው እየተፋለሙ ባሉባት አገር ሁኔታ በሀገር ቤት ይሄ ነው የሚባል በኢትዮጵያ አንድነት የተጠናከረ ህዝባዊ ድርጅት በሌለበት ስፍራ ዛሬ በግብጽና በቱኒዝያ ያለው አይነት ህዝባዊ አመጽ በአገራችን ውስጥ ቢነሳና በስልጣን ላይ ያለው አምባገነን የወያኔ አገዛዝ የቤን አሊን እግር ተክቶ ካገር ቢፈረጥጥ ፣ መንግሥት በሌለበት ፣ ሰራዊቱም ማዕከላዊ በሆነ እዝ በማይታዘዝበት ሁኔታ እነዚህ ገንጣይ ቡድኖች ለኢትዮጵያ ህልውና አብረውን ይቆማሉ ማለት እራስን ከማታለል ያለፈ ወይንም ስላለው ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤን ማጣት ካልሆነ በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም ። እነዚህ ሁለት ቡድኖች ለአመታት አላማቸውና ምኞታቸው አድርገው መሳሪያ አንስተው የተዋጉበትን የግንጠላ ናፍቆት በስልጣን ላይ ያለውን አገዛዝ ወደድነውም ጠላነውም መንግሥት በሌለበት ሁኔታ ክፍተት ሲያገኙ ህልማቸውን እውን ከማድረግ ይቆጠባሉ ማለት ዘበት ነው ። ይልቁንም የኛ አጋር ይሆናሉ እያሉ የሚሰብኩን ፣ አንድም ልዩ ተልዕኮ ያላቸው ፣ አሊያም

ኢትዮጵያዊነት ፌራርሶና ወዳድቆ ለማየት ጽኑ ምኞት ያላቸው ግለሰቦች ወይንም ቡድኖች በመሆናቸው ከጸረ ኢትዮጵያዊነት ውጪ ሊመደቡ አይገባም ።

በኢትዮጵያ ላይ ያንዣበበውን ጥቁር ጥላ እውን እንጂ ህልም አይደለም ። “ኋላ ከመማቀቅ ፣ አስቀድሞ መጠንቀቅ” እንዲሉ ፣ ማድረግ የሚቻል ነገር ካለ አስቀድመን ማድረግ እንድንችል ፣ የፈራነው እንዳይደርስ ለመከላከል ካልሆነ በቀር ፣ ሌሎች ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ስላሉት አመፃው ይቀራል ወይንም ይመጣልም ማለትም አይደለም ። የሚመጣውንም አመፃ የመግታት አቅም ያለው ግለሰብም ይሁን ቡድን አይኖርም ። አመጹ የራሱ ጊዜ ፣ የራሱ የሆነ ሂደትና እድገት ስላለው ፣ ከማናችንም ፍላጎትና ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ ተነስቶ ፣ የራሱን ሂደት ሄዶ ፣ የራሱን ክንዋኔ አከናውኖ ፣ የሚጠናቀቅ ይሆናል ።

እዚህ ላይ አንድ መዘንጋት የማይኖርበት አብይ ጉዳይ አለ ። የቱኒዝያው አመጽ በቀለጠፈና በፈጣን ሁኔታ መጠናቀቁ ይታወቃል ፣ ባንፃሩ ግን የግብፁ አመጽ የውጪ እጅ ጣልቃ ገብነት ስላለው መጓተት ይታይበታል ፣ ማለትም ሙባረክ የምዕራባውያኑ ታማኝ ሎሌ በመሆኑ ምዕራባውያኑ በቀላሉ ሊያጡት ባለመፈለጋቸው የተነሳ ህዝብን ለማታለል የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ እያየን ነው ። ነገር ግን የግብፅ ህዝብ የፈጀውን ይፈጃል እንጂ ድሉን እንደሚቀዳጅ የሚያጠያይቅ አይደለም ። እነዚህ የውጪ ኃይላት ሙባረክን ቢቻል በጥገናዊ ለውጥ እንዲቀጥል ባይቻል ግን ባምሳያው የነሱ አገልጋይ በሆነ ለመተካት የሚያደርጉት ርብርቦሽ የማታ ማታ ህዝብን አስቆጥቶ ነገሩ ወደነሱ ሊዞርና ከሚመኙት በተቃራኒው ሊያገኙ እንደሚችሉ አለመረዳታቸው ነው ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ህዝቡ በአንድነቱና በአገሩ ላይ ምንም የማያወላዳ አቋም ስላለው ትግሉን ሊቀለብሱ እንደማይችሉ መመስከር ይቻላል ። በተመሳሳይ ሁኔታ ግን ወደ እኛ አገር ስንመለስ በግብፅ የተከሰተው የምዕራባውያን ጣልቃ ገብነት ተላላኪያቸው መለሰን ለማዳን ዛሬም የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደማይኖር አስቀድሞ መረዳት ያስፈልጋል ። ይህ ሁኔታ ለኛ አዲስ አይደለም በ 1997 ምርጫ በነ ቪኪ ሀድልሰንና (Vicky Huddleston) በውስጥ አርበኞች ተባባሪነት የህዝብ እምቢተኝነት ሊቀለበስ ችሏል ። ዛሬም ህዝባዊ አመጽ ባገራችን ቢነሳ እነዚሁ ምዕራባውያን በአገራችን ጉዳይ ጣልቃ እንደሚገቡ መዘንጋት አይኖርብንም ። ስለሆነም ዛሬ ባለንበት የመከፋፈልና ያለመግባባት ከቀጠልን በሌሎች አገሮች ያየነውና የመሰከርነው ድል ባገራችን እውን ላይሆን እንደሚችል መገንዘብ የግድ ይላል ። ይህንን ጉዳይ ከቁም ነገር በማስገባት አንድነታችንንና ህብረታችን ላይ ከምን ጊዜውም በላይ መስራት እንደሚኖርብን አያጠያይቅም ፤ “ሳንቀደም መቅደም፡ እንደሚኖርብን ሳላሳስብ አላልፍም ።

በተለይ ከኢትዮጵያ ውጪ ሆነው አመጹ መነሳት አለበት በማለት የሚቀሰቅሱ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ፣ በየድረገጹና በየሬድዮ ጣቢያው እየቀረቡ ሲያቅራሩ አድምጠናል ። ከግብጽ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ተራ ነው ! ህዝቡን ለአመጽ ማነሳሳት ያስፈልጋል! እያሉ የሚሞነጫጭሩ የወረቀት ነብሮችንም ታዝበናል ። ይህ ግርግር አልኩ ከማለት አያልፍም ። አገር ውስጥ ለሚደረግ ትግል ፣ አገር ውስጥ ካለው ዜጋ በቀር የውጪው አዳማቂና አራጋቢ ከመሆን ያለፈ ምንም አስተዋጽዖ አይኖረውም ። የማያቃጥላቸውን እሳት ካልጭርን እያሉ ቡራ ከረዩ ማለትና ጎንበስ ቀና ማብዛት ፣ አመጽ አያስነሳም ፤ የተነሳም አመጽ ካለ የማቆም ቅንጣት ኃይል አይኖረውም ።

በአገራችን ያለው የጠባብ ብሄረተኛው አምባገነን መንግስት በህዝብ ላይ የሚያደርሰው ሰቆቃና ጭቆና ህዝብ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ እንደደረሰና አሁንም በቱኒዝና በግብጽ ገንፍሎ እንደተነሳው የህዝብ አመጽም በኢትዮጵያ ውስጥ በቅርቡ ሊነሳ እንደሚችል ምንም አጠያያቂ አይሆንም ። ነገር ግን የወያኔ አገዛዝ አንድም በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ ድርጅቶች እንዳይኖሩ በማድረጉ ፣ ቢኖሩም ወያኔ በመሀከላቸው ሰርጎ በመግባት አቅማቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲዳከም በማድረጉ በሚነሳው ህዝባዊ አመጽ ህዝብን ከስራቸው ለማሰባሰብና አመፃውን ለመምራት ያላቸው አቅም እጅግ የተመናመነ በመሆኑ ፣ አሁንም የተነሳውን ህዝባዊ አመጽ በመንተራስ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ዛሬ ጎላ ብለው የሚታዩትና እንቅስቃሴያቸውም የሚራገብላቸው ኢትዮጵያን አፈራርሰው የራሳቸው የሆነ የጎጥ መንግስት ለመመስረት የሚቋቋሙት የነዚሁ ጠባብ ብሄርተኞች ስብስቦች እንደሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም ። እነዚህም ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች ኦብነግና (ONLF) ፤ ኦነግን (OLF) ፤ ይጠቅሷል ። እዚህ ላይ ህወሃትንም (TPLF) መዘንጋት የዋህነት ይሆናል ።

የህዝብ አልገዛም ባይነትና አመጽ የአፄውን ስርአት ገርስሶ በጣለበት ወቅት ህዝብ ባደረገው ተጋድሎ በወቅቱ ይህ ነው የሚባል የተደራጀ ኃይል ባለመኖሩ የህዝብ ትግል በጦር ኃይሎች ተቀምቶ 17 የሰቆቃ አመታትን መሳለፉ ይታወቃል ። አሁንም አገር አቀፍ የሆነ ህዝባዊ ስብስብ እስከሌለ ድረስ የወያኔው አገዛዝ በህዝብ

አመጽ ተገፍቶ ቢወድቅ ተጠቃሚው ለጊዜው በአንድ ዓላማና እምነት ስር ተሰባስቦ የሚገኘው የግንጠላ ዓላማ ያላቸው የጠባብ ብሄረተኞች ባይሆኑም እንኳን እንደ አዜው ስርአት ዘር ፣ ጎሳና ሃይማኖት ሳይለይ የተቋቋመ የጦር ሰራዊት ሳይሆን በዘር መዋቅር የተደራጀ የጦር ኃይል እንዳለ መዘንጋት አይገባም ። ይህ ከአንድ ብሄር በተውጣጡ መኮንኖች የሚመራው የጦር ኃይል የሚነሳውን ህዝባዊ አመጽ አንድም ካሉት የግንጠላ ቡድኖች ጠለፋ ካመለጠ ፣ በሌላኛው ወገን ደግሞ የህዝብ ወገን ሊሆን የሚችል በአንድነት ስም የተሰባሰበ ይሄ ነው ተብሎ የሚጠቀስ ህዝባዊ ድርጅት ከሌለ ፣ እንደቀደመው ከአዜውን አገዛዝ በመጣል የተገኘውን ድል የምርጥ መኮንኖች ጥርቅም እራሱን ደርግ እያለ በሚጠራው እንደተቀማው ሁሉ ፤ ዛሬም የህዝብ ድል ከጦር ኃይሉ እጅ ሊወድቅ የማይችልበት ምንም አስተማማኝ ሁኔታ የለም ። በተለይ የጦር ኃይሉ የአንድ ብሄር መዋቅር በመሆኑ ሽግግሩ ከወያኔ ወደ ወያኔ "አልሸሹም ዞር አሉ" ወይም "ከእሳት ወደ እረመጥ" እንዳይሆንም ያሰጋል ።

ይህ ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ውስጥ መቼ ይነሳል? የሚል ጥያቄ በሁላችንም አይምሮ የሚጉላላ ቢሆንም ያንን መተንበይ ግን አይቻልም ፣ ሆኖም ግን ፣ እምብዛም እሩቅ እንደማይሆን መናገር ይቻላል ። ጭቆና ለዘመናት ስር በሰደደበት ስፍራ ሁሌም ህዝባዊ አመጽ መከሰቱ አይቀሬ ነው ። ያንን የሚያቀጣጥለው በነጮቹ አባባል (The last straw that broke the camel's back) እንዲሉ ፣ እንደ ቱኒዝያው ወጣት እራሱን በእሳት አቃጥሎ ህይወቱን እንዳጠፋውና ያ ለቱኒዝ ህዝባዊ አመጽ መንስኤ እንደሆነ ሁሉ ፤ ባገራችንም በተመሳሳይ ሁኔታ የአዜውን የገለማ አገዛዝ ተሸክሞ የኖረውን ህዝብ ያስቆጣውና ለአመጽ እንዲነሳሳ ያደረገው ብሎም አዜውን ከስልጣን ያስወገደው "ሴክተር ሪቪው" (Sector review) በመባል የሚታወቀውን የትምህርት ስርአት አሰጣጥ ዘይቤ ተግባራዊ ለማድረግ የነበረው እቅድ እንደነበር ይታወቃል ።

አሁንም በአገራችን አመጹን አቀጣጣይ ሊሆን የሚችለውን ቀስቃሽ ምክንያት ዛሬ መተንበይ ባይቻልም እያሌ የሆኑ ክብሪቶች እሳቱን ለመጫር ቀናቸውን እየጠበቁ እንደሆኑ የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርብ ሆኖ ለተመለከተ የተሰወረ አይሆንም ።

በማጠቃለያ የሚሆን ይሆናል ማናቸውም ነገር ከመሆን አያግደውም ፣ የማይሆን ደግሞ ወደድንም ጠላንም አይሆንም ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን በተለይ በሺዎች የሚቆጠር ማይል እርቀት ተቀምቶ ያለው ኢትዮጵያዊ ህዝብ ለአመጽ እንዲነሳ የማይሆን ጥሪ ከማድረግ ይልቅ ፤ አንድ ህዝብና አገር አቀፍ የሆነ ድርጅት በአገር ቤት እንዴት መፍጠር የሚቻልበትን ሁኔታ ላይ ቢመካከርና ጊዜውን በዚያ ለማሳለፍ ቢሞክር ይመረጣል ። በአገራችን ለውጥ እንደሚያስፈልግ ምንም አጠያያቂ አይደለም ። ግን ምን አይነት ለውጥ? ነው የሚሆነው ጥያቄው ። የህዝብ አመጽ አይቀሬ ነው እኛ ስለጠራን ስላልጠራን ሳይሆን እራሱ ነባራዊ ሂደቱ የሚያመጣው ነው ፤ ሆኖም ግን አብሮት የሚመጣ አላስፈላጊ አደጋም እንዳለ መገንዘብ የግድ ይላል <u>"የሚፈርስ ከተማ ፣ ነጋሪት ቢጎሰም አይሰማ"</u> የሚባለው ብሂል ባገራችን እንዳይተገበር የሁላችንንም እርብርቦሽ የሚጠይቅ ችላ ልንለው የማይገባ እንደሆነና ታሪካዊ ግዴታችንም መሆኑን አምነን ፣ ተቀብለን ፣ አገራችንን ከውድቀት እንታደጋት ።

ከድጡ ወደማጡ እንዳንገባ ነቅተን እንጠብቅ ።

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ !!
አምባገነኖች በተባበረ የሕዝብ አመጽ ይደመሰሳሉ!!

አይምሮ ዳኛቸው aymirod@yahoo.com